CAPITAL AREA FOOD BANK

# የእርሶ ውሂብ የእርሶ መብቶች

*ይህ ማጀት (pantry)ደንበኞች አገልግሎት ለማግኘት ሲመጡ የሚገቡበትን ስርዓት ወደ ኤሌክትሮኒክስ ስርዓት በመቀየር ላይ ነው። ይህ ማለት ቀደም ሲል በወረቀት ላይ ይሰበሰቡ የነበሩ ሁሉም መረጃዎች አሁን በኮምፒዩተር አሰራር ስርዓት ተይዘው ይቀመጣሉ ማለት ነው። ይህም ለዚህ ማጀት (pantry)፣ ለ Food Bank፣ እና ከሁሉም በላይ ለእርስዎ ትልቅ ለውጥ ነው! ከዚህ በታች የእርስዎን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክረናል። ይበልጥ ማወቅ ከፈለጉ፣ በአቅራቢያዎ በሚገኝ ማጀት (pantry) ውስጥ ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር እባክዎን ይወያዩ።*

## አዲሱ ሥርዓት ምንድን ነው?

ስርዓቱ **የአገልግሎት ዕይታዎች (Service Insights)** ተብሎ ይጠራል። ማጀቶች (pantries) ማህበረሰባቸውን በቀላሉ እንዲገነዘቡ/እንዲያውቁ እና አገልግሎታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያደርግ የዲጂታል አሰራር ስርዓት ነው።

በዚህ ማጀት ውስጥ ያሉ አንዳንድ ምግቦች TEFAP በተሰኘ ፕሮግራም ከፌዴራል መንግስት የሚገኙ ናቸው። በ TEFAP ፕሮግራም ምግብ የሚያገኙ ሰዎች የተወሰኑ የወረቀት ቅፆችን ሞልተው እንዲያጠናቅቁ መንግስት ይጠይቃል። የአገልግሎት ዕይታዎች (Service Insights) ተብሎ በተሰየመው ስርዓት፣ ያ ሂደት አሁን በኤሌክቶሮኒክስ ዘዴ ተሞልቶ ይጠናቀቃል። ለ TEFAP ብቁ መሆንዎን የሚገልጽ መረጃ በወረቀት ላይ ሳይሆን በኤሌክትሮኒክ ስርዓት ውስጥ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ የሚከማች ይሆናል።

መረጃዎን ከሰጡ በኋላ ያመለከቱበት ማጀት (pantry) የአሞሌኮድ (barcode) ካርድ ይሰጥዎታል። ይህ ማጀት (pantry) (እና የአገልግሎት ዕይታዎችን (Service Insights) የሚጠቀም ማንኛውም ሌላ ማጀት) በቦታው መገኘትዎን በፍጥነት መዝግቦ ለማስቀመጥ ይህንን ካርድ ስካን ሊያደርጉ ይችላሉ። የቱንም ያህል ማጀቶች (pantries) ቢጎበኙ የሚስፈልግዎት አንድ ካርድ ብቻ ነው፤ የአገልግሎት ዕይታዎች (Service Insights) ስርዓት መጎብኘት የሚችሏቸው የማጀቶች ቁጥርን ለመገደብ ዓላማ በፍፁም ጥቅም ላይ አይውልም።

## ምን ዓይነት መረጃ መስጠት አለብኝ?

የ TEFAP ምግቦችን ማግኘት እንዲችሉ፣ ስለእርስዎ እና ስለ ቤተሰብዎ አንዳንድ መረጃዎችን እንፈልጋለን፡-

- ሙሉ ስምዎን
- በቤትዎ ውስጥ የሚኖሩ የሰዎች ብዛት
- እንደ SNAP ወይም TANF ያሉ የተወሰኑ ለህዝብ የቀረቡ ጥቅማ ጥቅሞችን እያገኙ መሆኑን
- አድራሻዎን
- የቤተሰብዎን ገቢ

እንደ የአመጋገብ ምርጫዎችዎ፣ ያሉ ሌሎች መረጃዎችን እንጠይቅዎታለን፣ ነገር ግን ይህ እንደ አማራጭ የሚቀርብ ሲሆን በ TEFAP ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ አያሳድርም ።

## ለውጡ ለምን አስፈለገ?

ይህ ማጀት (pantry) ደንበኞች ከማጀቱ አገልግሎት ለማግኘት የሚመዘገቡበትን እና የሚገመገሙበት አሰራር ሂደት ለማቃለል ከ Capital Area Food Bank ጋር እየሰራ ነው። ስለእራስዎ እና ስለቤተሰብዎ ጥቂት ጥያቄዎችን በመመለስ፣ ይህ ማጀት (pantry) እርስዎን ለማገልገል ብዙ ጊዜ እንዲወስድ እና የወረቀት ስራዎችን በመስራት ጊዜ እንዳያባክን ይረዳሉ። ይህ ማጀት (pantry) ገንዘብ ለማሰባሰብ እና ስራውን ለማህበረሰቡ ለማስተዋወቅ እንዲረዳው አገልግሎት የሰጣቸውን ሰዎች ቁጥር እንደማሳያ ሊጠቀም ይችላል።

## ይህን በየግዜው ማድረግ አለብኝ?

አይ የለብዎትም፣ የአገልግሎት ዕይታዎችን (Service Insights) መጠቀም መረጃዎን በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንድናከማች እና ወደፊት መረጃዎቹን ስንፈልግ በፍጥነት ማግኘት እንድንችል ይረዳናል።

በየጊዜው መረጃዎን እንዲያረጋግጡ እና እንዲያዘምኑ ብቻ እንጠይቅዎታለን። ለ DC እና Maryland ነዋሪዎች በየዓመቱ፣ እንዲሁም ለ Virginia ነዋሪዎች በየሁለት ዓመቱ  ለ TEFAP ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ ዘንድ ይጠየቃሉ።

# የእርሶ ውሂብ የእርሶ መብቶች

## የ CAFB ውሂብ ቃልኪዳን

**እርስዎን እና መረጃዎን በማዕረግ እና በአክብሮት እንይዛለን።**

ሁሉም ምላሾችዎ በምስጢር ይያዛሉ። የእርስዎን መረጃ መስጠት ካልፈለጉ ወይም መመለስ ምቾት የማይሰጥዎ ማንኛውም ጥያቄ ከቀረበልዎ፣ ምንም ይሁን ምን እርስዎአገልግሎቶችን ማግኘትዎ አይቀርም። የእርስዎን መላሾች አምነን እንቀበላለን፣ እንዲሁም ላለመሳተፍ ከመረጡ ከሌሎች በተለየ መንገድ አንይዝዎትም። በአገልግሎት ዕይታዎች (Service Insights) ላይ መሳተፍ ካልፈለጉ፣ የብቁነት መረጃዎን በወረቀት ቅፅ ላይ ለመስጠት መምረጥ ይችላሉ።

**የእርስዎን መረጃ ደህንነቱ በተጠበቀ እና በአስተማማኝ መንገድ እንይዛለን።**

በዘርፉ በጣም ውጤታማ እና ወቅታዊ የሆኑ የመረጃ ደህንነት አጠባበቅ እርምጃዎችን በመጠቀም መረጃዎ የሚከማች ይሆናል። በግዛትዎ ውስጥ የሚገኝ TEFAP ን የሚቆጣጠር ኤጀንሲ የሚያቀርበውን ጥያቄዎች ለመመለስ ካልሆነ በስተቀር የእርስዎን የግል፣ የተናጠል መረጃ ከዚህ አጋር አውታረ መረብ ውጭ ለሆነ ለማንም አናጋራም። የአገልግሎት ዕይታዎች (Service Insights) በጣም ከፍተኛ የደህንነት ጥበቃ ስታንዳርዶች ያሉት ሲሆን፣ ተጠቃሚዎች ማየት የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ብቻ ነው ማየት የሚችሉት። መረጃን በዚህ መንገድ መዝግቦ መያዝ በወረቀት ላይ ከመመዝገብ የበለጠ አስተማማኝ ነው። የእርስዎን የግል መረጃ እንደ ህግ አስከባሪ አካላት ወይም የኢሚግሬሽን አገልግሎቶች ላሉ ኤጀንሲዎች **በጭራሽ** አናጋራም።

**ይህንን መረጃ የምንጠቀመው ለእርስዎ የተሻሉ አገልግሎቶችን ለመስጠት ብቻ ነው።**

መሰረታዊ የሆኑ መረጃዎን ለእኛ በመስጠት፣ አገልግሎቶቻችን በተቻለን መጠን ከማህበረሰቡ ፍላጎቶች የተጣጣሙ ለማድረግ እንድንችል ይረዱናል። የእርስዎን ግላዊ እንቅስቃሴ ለመከታተል ወይም ለእርስዎ የምንሰጣቸውን አገልግሎቶች ለመገደብ ይህንን መረጃ ጥቅም ላይ አናውልም። የምግብ ባንኩ (The Food Bank) የእርስዎን መረጃ ለገበያ ወይም ለንግድ ዓላማ ፈጽሞ አይጠቀምም። የእርስዎን መረጃ የሚከፍት ማንኛውም ሰው ይህን የሚያደርገው እርስዎ ያገኙትን አገልግሎቶች ለመመዝገብ ወይም መግለጫዎን ለማዘመን ብቻ ይሆናል። የእርስዎ ማጀት (pantry) እና የምግብ ባንኩ (the Food Bank) አዝማሚያ/ዝንባሌዎችን ለመለየት እና ስለ ማህበረሰቡ የበለጠ ለማወቅ ሪፖርቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። እነዚህ ሪፖርቶች በግል የእርስዎን ማንነት ለይቶ ሊያሳውቁ የሚችል መረጃን በጭራሽ አያሳዩም።

***ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካልዎት?***

በ www.capitalareafoodbank.org/insights *ይጎብኙ ወይም በኢሜይል አድራሻ*ServiceInsights@capitalareafoodbank.org ላይ መልዕክት ይላኩ።